ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ሐምሌ 1999 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ቁጥር 9

# የገጠር መሬትና የመሬት ገበያዎች

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## መግቢያ

ከ1967ቱ ሥር ነቀል የመሬት አዋጅ ጀምሮ መሬት ለኢትዮጵያ አርሶ አደር ዋነኛ «ንብረት» ነው:: ይህ አዋጅ ሲታሰብ በወቅቱ የነበረው ህብረተሰብ፣ በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች አገራዊ እንቅስቃሴአቸው (አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ)ና መሪ መፈክራቸውን "መሬት ለአራሹ" ማስታወስ ተገቢም አስፈላጊም ነው፤ አዋጁ የፈጠረውን ከፍተኛ አገራዊ ደስታና ተስፋም ማስታወስ እንዲሁ አስፈላጊ ነው:: ይህ ደስታና ተስፋ የተፈጠረው አዋጁ ፊውዳላዊና በዝባዥ የሆነውን የመሬት ስርአት እንዲያከትም በማድረጉና ገበሬው የመሬቱ ሙሉ ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ባለቤት አድርጎታል በሚል ነበር:: አዋጁ ገበሬውን የመሬቱ ባለቤት አድርጎታል፤ የመሬት ጥያቄም መሠረታዊና በቂ መልስ አግኝቷል ብሎ በማሰብም የገጠር መሬት ጉዳይ ዳግመኛ ብሔ ራዊ አጀንዳ እንደማይሆን ተገምቶም ነበር::

የገጠር መሬት ጉዳይ ግን አሁን ድረስ ዋነኛው ብሔራዊ የልማትና የፖለቲከ ጥያቄ ሆኖ ቀጥሏል:: እንደውም አወዛጋቢነቱና ወቅታዊነቱ እየጨመ ረ ብቻ ሳይሆን ጥያቄው ይበልጥ የእምነት ጉዳይ የመምሰል ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ይህም የገጠር መሬት ጥያቄ በመሠረቱ የልማትና የኢኮኖሚ እንዲሁም የዜጎች የመብት ጉዳይ ሆኖ መፍትሄው ግን እነዚህኑ ጉዳዮችና ያለፈውን ተሞክሮአችንን መሠረት ባደረጉ ጥናቶችና መረጃዎች ላይ በተመሠረቱ እውነተኛ ውይይቶች፣ ከዛም ፓለቲካዊ በሆኑ ሂደቶችና ውሳኔዎች መልስ ማግኘት እንዳለበት የሚያሳየውን የሰለጠነና ሳይንሳዊ የችግሮች የአፈታት ሥርአት እንዳንከተል አድርጐናል::

የ1967ቱ ሥር ነቀል የገጠር መሬት አዋጅና ከዛም በኋላ በተለይም ከ1983ቱ የመንግስት ለውጥ በኋላ በተ ወሰኑ ጉዳዮች ላይ የተወሰዱ የተለያዩ እርምጃዎች የገጠር መሬት ጥያቄው መሠረታዊ ብሄራዊና አወዛጋቢ አጀንዳነቱን ይዞ እንዳይቀጥል ለምን አላስቻሉም? የሚከተሉት ሶስት ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ::

**1ኛ.** በምግብ ችግርና በድህነት ኑሮአቸውን የሚገፉ አርሶ አደሮች ብዛት ሊቀንስ አለመቻሉ እንዲያውም በተቃራኒው እየጨመረ መሄዱ፤ ይህም አብዛኛው ገበሬ ሌላውን ሊቀልብ ቀርቶ የራሱን /የቤተሰቡን/ ፍጆታ ለመሸፈን አለመቻሉን ያሳያል:: ለምሣሌ የኢትዩጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር በ2004 ባደረገው ብሄራዊ ጥናት በጥናቱ ከተሳተፉት ሁለት ሶስተኛው ገበሬዎች የሚያመርቱት ምርት ለራሳቸው በቂ ባለመሆኑ ሸማች ገበሬ ዎች (Net buyers of food) መሆናቸውን ይገልፃል:: በተጨማሪም በአማካይ አንድ አርሶ አደር ራሱንና ቤተሰቡን ከድህነት ለማውጣት ከሚያስፈልገው ገንዘብ በወቅቱ ከእርሻ ሥራ ያገኝ የነበረው 59% ብቻ ነው:: ይህም በወቅቱ በነበረው ምርታማነትና ዋጋ አንድ ገበሬ በአማካይ 2.8 ሄክታር የእርሻ መሬት እንደሚያስፈልገው ያሳያል:: እነዚህን መሰሉ እውነታዎች በኢትዮጵያ ልማት ጉዳይ ላይ የሚመራመሩ ተ ማራማሪዎች፣ እርዳታ አድራጊዎችና ሌሎችም የአገሪቱ የመሬት ፓሊሲ በዚህ ሁኔታ ላይ አስተዋፅኦ አለው ብለው እንዲያምኑ በማድረጉ::

**2ኛ.** በመሬት ጉዳይ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ከምርምርና ልምድ በተገ ኙ መረጃዎች ከመታገዝ ይልቅ ጉዳዩ ከፍተኛ የፓለቲካ አትኩሮት በመሳብ በመረጃ ላይ የተመሠረተ የሠከነ ውይይት ማድረግ አስቸጋሪ ማድ ረጉ፤ ይህም ብዙ ሰዎች በጣም ጠቃሚ በሆነው በመሬት ጉዳይ ላይ ውይይት ለማድረግ ያላቸውን ፍላጐት እየገታ መምጣቱ::

**3ኛ.** ገበሬው አሁን ባብዛኛው መደበኛ ባልሆነ መልኩ የሚጠቀምበት የመሬት ገበያ (ቁርጥ ኪራይ ፣ቁርጥ ያልሆነ ኪራይና ወለድ አግድ) ላይ ያለን ዕውቀት ውሱን መሆኑ፤ ይህም

ከዚህ የመሬት ገበያ ተሞክሮ በመመስረት ሶስት አሥርተ ዓመታት ያሳለፈውን የመሬት ፓሊሲው ላይ የምናደርገውን ውይይት የዳበረ እንዲሆን የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል።

ይህ ጥናት በ1996 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር) የነበ ረውን የመሬት ገበያ በማጥናት ይህን የመሬት ገበያ ለማሻሻልና ከዛም አልፎ በመሬት ፓሊሲአችን ላይ ያለውን እንድምታ በመለየት የመነሻ የፓሊሲ ሃሳቦችን ለማቅረብ የተደረገ ነው።

ጥናቱ ከጋምቤላ ብሄራዊ ክልል ውጭ በሁሉም ክልሎች የሚኖሩ ከ4500 የሚበልጡ አርሶ አደሮችን በዝርዝር በማነጋገርና በማወያየት በ1996 በተሰበሰበ መረጃ የተመሠረተ ነው። የጥናቱ ውጤት የማህበራዊ ጥናት መድረክ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስና የግብርና አኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበራት በ1997 በጥምረት ባዘጋጁት አውደ ጥናት ሰፊ ውይይት ተካሂዶበታል።

## 2. የጥናቱ ግኝቶች

### *2.1 የመሬት ገበያ ስፋትና ሁኔታ*

ጥናቱ እንደሚያመለክተው በአገር አቀፍ ደረጃ በመሬት ገበያ የተሳተፉ ገበሬዎች ብዛት በመቶኛ 13.4% ናቸው። የመሬት ገበያው በአማራና ትግራይ ክልሎች በስፋት ይካሄዳል። በአማራ 23% እና በትግራይ 22% የሚሆኑ ገበሬዎች (በመሬት ገበያው አማካኝነት) የሌላ ሰውን መሬት አርሰዋል። ይህ አሃዝ በኦሮሚያ 13.3%፣ በደቡብ 4% እና በሌሎች ክልሎች 7.8% ነበር። በሌላ በኩል በመሬት ገበያው አማካኝነት ለገበያ የቀረበው ጠቅላላ የመሬት ስፋት (በወቅቱ ከታረሰው ጠቅላላ መሬት አንፃር) በትግራይና ኦሮሚያ 19%፣ በአማራ 22% ሲሆን በደቡብ 5% እና በሌሎች ክልሎች 17% ነበር። በአጠቃላይ እነኚህ መረጃዎች የመሬት ገበያው (ከሽያጭ በመለስ ያለው) የተስፋፋ መሆኑን እንዲሁም በገበያው የሚሳተፉ ገበሬዎችንና ጠቅላላ ኢኮኖሚውን በተሻለ መልኩ የሚጠቅም ፓሊሲን የመኖር (ወይም የማሻሻል) አስፈላጊነትን ይጠቁማሉ።

የመሬት ኪራይ ዋጋ እንደየኪራዩ አይነት ይለያይ ነበር። ቁርጥ ባልሆነ መልኩ (Sharecropping) የሚከራዩ ገበሬዎች በአማካይ ከሚያመርቱት ምርት በኦሮሚያ 47%፣ በትግራይ 49%፣ በአማራ 48% እና በደቡብ 54% ይከፍሉ ነበር። በቁርጥ ኪራይ የሚከራዩ በሄክታር በትግራይ 640 ብር፣ በደቡብ 653 ብር፣ በኦሮሚያ 416 ብር፣ እንዲሁም በአማራ 384 ብር ይከፍሉ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። እነኚህ መረጃዎች መሬት በአንፃራዊ መልኩ በትግራይና በደቡብ ውድ መሆኑን ቢያመለክቱም በአጠቃላይ መሬት ውድ አልነበረም። ይህም በወቅቱ የነበረውን ዝቅተኛ ምርታማነትና (አሁንም በሚታይ መልኩ ተ ለውጧል ማለት አይቻልም) ዝቅተኛ የምርት/የሰብል ዋጋን ያንፀባርቃል።

አማካይ የኪራይ ጊዜ (ለቁርጥ ኪራይ fixed rental) በትግራይ፣ አማራና ኦሮሚያ 3 ዓመታት (ተ ከታታይ) ሲሆን በደቡብ 4 ዓመታት ነበሩ። ቁርጥ ላልሆነ ኪራይ (Sharecropping) ደግሞ በትግራይና ደቡብ ክልሎች በአማካይ 2.6 ዓመታት፣ በአማራ 4.5 ዓመታትና በኦሮሚያ 3.3 ዓመታት ነበሩ።

በአንድ የመሬት ግብይት ወቅት በቁርጥ ኪራይ ከአከራይ ወደ ተከራይ የተላለፈውን መሬት ስፋት በተመለከተ ከአከራዮችና ተከራዮች የተሰበሰበው መ ረጃ መጠነኛ ልዩነት ይታይበታል። በአራቱ ትላልቅ ክልሎች የሚገኙ አከራዮች በአማካይ ያከራዩት መሬት ከ0.25 እስከ 0.65 ሄክታር እንደሚደርስ፣ ከተከራዮች የተገኘው መረጃ ደግሞ ከ0.64 እስከ 0.98 ሄክታር መሬት መከራየታቸውን ያሳያል። ይህ ልዩነት አንድ ተከራይ ከተለያዩ ከአንድ በላይ ሰ ዎች ተከራይቶ/ታ እንደነበር ወይም አከራዮች ያከራዩትን የመሬት ስፋት ቀንሰው ሪፖርት አድርገው ሊሆን ይችላል። ይህም በብዙ ክልሎች ገበሬዎች ያላቸውን በሙሉ መሬት ማከራየት እንደማይችሉ ከሚደነግገው ፓሊሲ/መመሪያ አንፃር ትክክል ሊሆን የሚችል ግምት ነው።




## 3. ሌሎች ዋና ዋና ግኝቶች

- መሬት የሚከራዩ አርሶ አደሮች የተሻለ የሰው ጉልበት ያላቸዉ ናቸው። ለምሣሌ ያህል በቁርጥ ኪራይ የሌላ ሰው መሬት የሚያርሱት በአማካይ (ከአከራዮቻቸው አንፃር) የ20% የተሻለ የሰው ጉልበት ሲኖራቸው፣ ቁርጥ ባልሆነ ኪራይ የተ ከራዩት ደግሞ የ30% የተሻለ የሰው ሃይል (adult labor) ነበራቸው።
- የመሬት ገበያም መሬት ከአረጁ ሰዎች ወደ ወጣቶቹ፣ ከታመሙ ወደ ጤነኞቹ በማስተላለፍ ረገድም ቁልፍ ሚና ይጫወታል። የጥናቱ ውጤ ት እንደሚያመለክተው መሬት ተከራዮች በአማካይ ከአከራዮቻቸው በ8 ወይም በ9 ዓመት የሚያንሱ ናቸው። በተመሳሳይም ጥናቱ ከመካሄዱ 12 ወራት በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ታሞ መተኛት ቁርጥ ባልሆነ መንገድ አከራዮች ዘንድ በ20% ቁርጥ በሆነ መንገድ አከራዮች ደግሞ በ34% ከፍ ያለ ነበር።
- በመሬት ገበያው ግልፅ የፆታ ልዩነት ይታያል። ሴቶች በአብዛኛው አከራዮች ናቸው። በመከራየት

ረገድ ሴቶች የ4% ድርሻ ሲኖራቸው በማከራየት ግን የ30% ድርሻ ነበራቸው፡፡

- የመሬት ገበያው የጉልበት ገበያውን (Labor Market) አነቃቅቷል፡፡ መሬት ተከራዮች (መሬት ካላከራዩት አንፃር) በሁለት እጥፍ የሚበልጥ የቤተሰብ ያልሆነ የሰው ጉልበት ተጠቅመዋል/ቀጥ ረዋል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ መሬት በአብዛኛው በምግብ ራሳቸውን ከአልቻሉት ወደ ቻሉት እንደሚተላለፍ ያሳያል፡፡ በአማካይ ቁርጥ ባልሆነ መንገድ ከአከራዩ ቤተሰቦች 73%ቱ የምግብ ደኅንነት ዋስትና ችግር (food insecure) ያለባቸው ነበሩ፡፡ በተመሳሳይም ከመሬት ተከራይ ቤተሰቦች ውስጥ 47% እንደዚሁ የምግብ ደህንነት ዋስትና ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ በቁርጥ ኪራይ መሬት የተከራየ ገበሬ በአማካይ የ6 ኩንታል ትርፍ ምርት (surplus production) ባለቤት የነበረ ሲሆን አከራዩ ግን በአማካይ የ3.2 ኩንታል ጉድለት ይታይበት ነበር፡፡



ሠንጠረዥ 2. የማዳበሪያ አጠቃቀም መሬት በአከራዩና በተከራዩ ገበሬዎች ዘንድ

- ጥናቱ እንደሚያሳየው አከራዮች ለአንድ ሄክታር መሬት ያገኙት ከፍተኛ የኪራይ መጠን ብር 653 የነበረ ሲሆን ተከራዮች ደግሞ ከመሬት ኪራይ ውጭ ያለውን ወጪ ሁሉ ሸፍነው ያገኙት አነስተኛ አማካይ ገቢ ብር 1434 ነበር (ከፍተኛው ገቢ ደግሞ ብር 4669 ነበር)፡፡ ይህ የሚያሳየው የመሬት ኪራይ በጣም ዝቅተኛ እንደነበር ነው፡፡ ከከፍተኛው የኪራይ መጠን (ብር 653) አንፃር አነስተኛው የኪራይ መጠን እስከ ሁለት እጥፍ ማደግ እንደነበረበት ወይም እንዳለበት መረጃው ያሳያል፡፡
- ይህ መረጃ 1ኛ- የመሬት ገበያው ፉክክር የሌለበት (uncompetitive) መሆኑን፣ 2ኛ በመሬት ገበያው ተሳታፊዎች (አከራይና ተከራይ) አንፃር ገበያው አንዱን ወገን (አከራዮችን) አላግባብ የሚጐዳ እንደነበር ያሳያል፡፡ ሆኖም አከራዮች በምንም ምክንያት መሬታቸውን ማረስ የማይችሉ ከነበሩ (if the opportunity cost of their land was zero) ያገኙት የኪራይ ገቢ ምንም ትሁን የመሬት ገበያው ሁለቱንም ጠቅሟል ማለት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የጥናታችንን ደረጃ ከቤተሰብ (አከራይና ተከራይ) ወደ ማህበረሰብ ደረጃ ከፍ ካደረግነው የአከራዩ ሰዎች ምንም አይነት ዋጋ ለተከራዮቻቸው ይክፈሉ ለማህበረሰቡ በተከራዩት መሬት ላይ የተሻለ ምርት በማምረት ህብረተሰቡን በተሻለ ደረጃ መጥቀም ችለዋል፡፡
- የመሬት ገበያው ምርታማነት ከፍ እንዲል ይረዳል፡፡ ይህም ዘመናዊ የምርት ግብአቶችን አጠቃቀም ከፍ እንዲልና የምርት (መሬት የሰውና የበሬ ጉልበት) ጥምረት የተሻለ እንዲሆን ምክንያት በመሆን ነው፡፡ መሬት ከተከራዩ ገበሬ ዎች ውስጥ 78%ቱ ዘመናዊ ማዳበሪያ ሲጠቀሙ በአማካይ በአንድ ሄክታር ላይ 170 ኪሎ ግራም ማዳበሪያ ተጠቅመዋል፡፡ እነኚህ አሃዞች ከመሬት አከራዮች ጋር ሲወዳደር በተጠቃሚዎች ብዛት በ24% በአጠቃቀም (በሄክታር) ከ100 ኪ.ግ በላይ የተሻሉ ናቸው፡፡
- የመሬት ገበያው ባክኖ ሊቀር የሚችል የሰውና የበሬ ጉልበት በእርሻ ሥራ ላይ እንዲውልም ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሬት አከራዮች ዘንድ ያለው የሰው ጉልበትና የመሬት ጥምረታ ከተከራዮቹ አንፃር 63% ብቻ ሲሆን የበሬ ጉልበትና የመሬት ጥምረታቸውም ከአከራዮቹ በ44% ያንሳል፡፡



ሠንጠረዥ 3. ምርታማነት መሬት በአከራዩና በተከራዩ ገበሬዎች ዘንድ

በአጠቃላይ የመሬት ገበያው ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ጥናቱ ያሳያል፡፡ ለምሣሌ:-

- መሬት ተከራዮች ከአከራዮች አንፃር በመሬት ላይ በአማካይ በ52% የበለጠ ወጪ (Short term investment) አውጥተዋል፡፡
- የመሬት ገበያው ዜጐች ድህነትን እንዲዋጉ እንዲሁም የተሻለ ምርት ለህብረተሰቡ እንዲመ ረት/እንዲቀርብ የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ የመሬት ተከራዮች አማካይ የሰው ጉልበት ምርታማነት (Labor Productivity) ከመሬት አከራዮች አንፃር በ64% የተሻለ ሲሆን መሬት ተ ከራዮች ከተመሳሳይ የመሬት ስፋት ላይ ያገኙት ገቢ በ24% የተሻለ ነበር፡፡
- ሆኖም የመሬት ገበያው በአብዛኛው ውድድር የሌለበት (uncompetitive) ከመሆኑ በላይ በተ ከራይና አከራይ መሃል ያለው ግንኙነት የብዝበዛ መልክ የሚታይበት ይመስላል፡፡ በዚህ ግንኙነት በአብዛኛው ተጠቂ የሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች በሴቶች (እማወራዎች)ና በአዛውንቶች የሚመሩ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የዚህ ምክንያቱ እነዚህ ቤተ ሰቦች በአብዛኛው አከራዮች በመሆናቸውና በወቅቱ ከኪራዩ የሚያገኙት ገቢ ያከራዩትን መሬት ቢያርሱት ከሚያገኙት ገቢ አንፃር እስከ 1/4ኛ ዝቅ ያለ ስለነበር ነው፡፡

## የፓሊሲ ጠቋሚ ሃሳቦች

- ፓሊሲ የሚነድፉ አካሎች የመሬት ገበያው ውድድር የሰፈነበት ገበያ እንዲሆን የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማድረግ ይኖርባቸዋል:: አሁን የሚካሄደው የመሬት ምዝገባና ሰርተፍኬት መርሐ-ግብር ያሉበትን ክፍተቶች አሟልቶ ከመቀጠል ባሻገር የመሬት ክፍፍል (redistribution) ከዚህ በኋላ እንደማይካሄድ በግልፅ መደንገግ ወይም ከተካሄዱ ሊካሄድ የሚችልበትን ጊዜና ሁኔታ (የቻይናን ልምድ በመመርኮዝ) መደንገግ፣ እንዲሁም ለኢንቨስትመንት ወይም ለሌላ ጉዳይ መሬት ከገበሬዎች ወደሌሎች የሚተላለፍበት ሁኔታ ግልፅነትና መተማመን ያለበት ማድረግ፣ የመሬት ገበያውን በማስፋትና (ከኪራይ ጊዜ፣ ከኪራይ ዋጋ ወዘተ አንፃር) ውድድር ያለበት በማድረግ አከራዮችንም ሆነ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ይበልጥ የሚጠቀሙበትን ሁኔታን ያመቻቻል::
- አንዳንድ የመሬት ገበያውን የሚገድቡ አሠራሮች ለምሣሌ የሚከራይ መሬትን ስፋትና የኪራይ ጊዜን የመገደብ ሁኔታዎች የመሬት ገበያው እንዳይስፋፋና እንዳይጠናከር በማድረግ አከራዮችንም ሆነ ኢኮኖሚው ይበልጥ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ስለሚያደርጉ እነኚህን እግዶች ማንሳት ወይም ማሻሻል ይገባል:: በጣም ትንሽና ምርታማነቱም አነስተኛ በሆኑ መሬቶች ላይ የሚካሄድ የመሬት ገበያን መገደብ ብዙ ጠቃሚ አይደለም:: መገደብ ካስፈለገም አንድ ተከራይ ሊያለማ ወይም ሊከራይ የሚችለውን ከፍተኛ የመሬት ስፋት ጣሪያ መወሰን ይሻላል::
- በገጠር ያለው እርሻ ነክ ያልሆነው የሥራ ክፍል እስኪነቃቃ ድረስ የመሬት ገበያው

  * ድህነትን (በህብረተሰብ ደረጃ) ና የመሬትና የጉልበት ምርታማነትን እንደሚያሻሽል፣
  * በገጠር ከመሬት እጦት/ጥበት እርሻ ነክ ሥራዎች ባለመስፋፋትና ብድር በማጣት የሚፈጠሩ ችግሮችን በተወሰነ ደረጃ በማርገብ፣ እንዲሁም
  * አዲሱን የመንግስት ገበያ ተኮር የእርሻ ፓሊሲን (Agricultural commercial-ization) እንደሚያጠናክር አማራጭ መታየት ይኖርበታል::

- ስለዚህ የመሬት ፓሊሲው አሁንና ወደፊት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ካለውና ከሚኖረው ችግር አንፃር ማሻሻል እንጂ ከመሬት አዋጁ (ከ1967) በፊት የነበረውን መሠረታዊ ችግር በመፍራት ፓሊሲውን (በተገቢው ደረጃ) ከማሻሻል መታቀብ ተገቢ አይደለም::

ሳሙኤል ገ/ሥላሴ (ዶ/ር)

**ምንጭ:-** *Samuel G/Sellassie*. Experiences in Land Rental Markets in Ethiopia: Impact on Equity, Efficiency and Poverty. In *Land and the Challenge of Sustainable Development in Ethiopia*, edited by Dessalegn Rahmato and Taye Assefa. Conference Proceedings. FSS, 2006.

**Acknowledgement & Disclaimer**

*This document has been produced with the financial assistance of the European Union. The contents of this document are the sole responsibility of the author and can under no circumstances be regarded as reflecting the position of the European Union.*

አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-157 29 90/91 ♦ ፋክስ: 011-157 29 79
ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et